# የህሊና ጉንተላዎች

ቤዝ አሲምባ ፀለምት - ዶሎኪያ ተርናሻ

መሰረት ያኖርኩት - መነሻ መድረሻ

አንዱን ላውሬ ጥሎ - ሌላዋን ለውሻ

ስደት አድርጎታል - ህይዎቴን መሸሻ።

* * * *

እናንት ወንድሞቼ

እናንት እህቶቼ

ጠላት አሰፍስፎ - ሰውርና ይፋ

ንቁ አናንቀላፋ

እኛም ዝምታውን - አበዛነው መሰል

ሁሉም ያነደናል እንደ ድንጊያ ከሰል።

* * * *

እንካ ባለክራር……

ግጥም ተቀበለኝ

ፍትህ የተጠማሁ - ነፃነት የራበኝ

ዕዝልና አራራይ - አድርገህ አዚመው

ወደ ላይ ወደ ታች - አንሳውና ጣለው

ቃኘው ባለክራር……

ቼ- በለው ቼ - በለው

ልቤን ማርከውና - በሙዚቃ አስክረው

በክራርህ ቅኝት - በጣቶችህ ጫፍ ላይ

ስመኝ እኖራለሁ - በህይዎቴ ድል ላይ።

* * * *

በክፉው ዘመን ወቅት - በዚያ በዘግናኙ

በነፃነት ትግል - ገብተው እየዋኙ

ለተበደሉና አቅመ ቢስ ለሆኑት

ጠበቃ እየቆሙ - ህይዎት ለከፈሉት

ነግ ከነገ ወዲያም - እሰከ ዘለዓለሙ

ማስታዎሻ ይሁን - የደም ቀይ ቀለሙ።

* * * *

የሚተካን ትውልድ - ዐይኑ የታወረ

በዘር ሃረግ መንገድ - ጥምል እየዞረ

የመንደርተኛ ቡን - በጎጥ እየጠጣ

ጫት ያመነዥካል - ቅጠል እንደ ጠጣ።

* * * *

ተማምለን ነበር - ፍፁም ነው ዕምነቴ

ቃልኪዳን ነበረን - ትግሉ ነው ሕይዎቴ

ማተቡን ፈትቶ - ከሃዲ ከዳና

አስገብቶን ጠፋ - በደም ባህር ዋና።

* * * *

ኢሕአፓ ሲገደል....

ለምን ሞተ ቢሉ

ታሪኩን በነቂስ ንገሩ ለሁሉ

ያብዮት ዘመቻ ሞት - ያረገው ስንቁን

የሕዝብ ድርጅት…… ቀይ ሽብር ይልቁን

እርሱን ብቻ ነበር - ከዜጎቹ አብልጦ

ቋጥሮ የተሸኘው - ኢትዮጵያዊ መርጦ።

* * * *

አንቺ የፀደይ አበባ….

የንቦች ቀሰም አጥቢያሽ

ፍንድቁ ሲፈካ ቦራሽ

የፀደይ ጥባቱ ፀዳል

ጨፈጉ ፈተት - ቧ- ሲል

ለኛ ነጋ መስከረም ጠባ

አደዮው ፈካ ፈነጠቀ

ያንቺው ጀንበር ግን ጠለቀ።

* * * *

ሞተዋል ይሉናል - ከሞትን ባገሩ

ህዝቡ ከቀበረን - ከተሜው ገጠሩ

ኢሕአፓ ሲነሳ - የ ‘ሞተ‘ አካል ፈርተው

ቀን ሲደነግጡ - ሌሊት እንቅልፍ አተው

ለምን ይኖራሉ - ዘወትር ባትተው ?

* * * *

ሸበቶውን ዘመን - ግንደ ቆርቆር ሆኖ

በዘመናት ትግል - በውስጡ ሸፍቼ

ፉሸሸቱን አገዛዝ - ቋያ እሳት ለኩሼ

በሰደድ-ነበልባል - አመፅ ተሟግቼ

የዘሩን ዘመን ግን - እግሬ ነቅሎ ሂዶ

ሳርር እገፋዋለሁ - ውስጥ አንጀቴ ነዶ !!

ግንቦት 2002

abraham beyenne